**ቀን፡ ጥቅምት 11 2018 ዓ.ም**

## <u>የስብሰባ ጥሪ ለያያ የክፍያ ስርዓቶች አ.ማ. ባለአክስዮኖች በሙሉ</u>

## <u>የባለአክስዮኖች 2ኛ መደበኛ እና 1ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ</u>

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድ ህግ አንቀጽ 366(1)፣ 367(1) ፣ 370፣ 400 እንዲሁም በአክሲዮን ማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀፅ 17 መሰረት የያያ የክፍያ ስርዓቶች አ.ማ. የባለአክስዮኖች 2ኛመደበኛ እና 1ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ሕዳር 6 ቀን 2018 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ጀምሮ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ/online/ የባለአክስዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተጠቀሰው ቀን፣ሰዓት እና ቦታ በጉባዔው ላይ እንዲገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

1. **<u>አክስዮን ማህበሩን የሚመለከቱ ዋና ዋና መረጃዎች</u>**
    - 1.1 የአክስዮን ማህበሩ ስም:- ያያ የክፍያ ስርዓቶች አ.ማ
    - 1.2. የአክስዮን ማህበሩ ዓይነት:- በክፍያ ስርዓቶች ሥራ ላይ የተሠማራ
    - 1.3 የአክስዮን ማህበሩ የምዝገባ ቁጥር:- MT/AA/3/0056125/2016
    - 1.4.የአክስዮን ማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት አድራሻ:- አዲስ አበባ፣ ቂርቆስ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 09 የቤ/ቁ. አዲስ
    - 1.5 የአክስዮን ማህበሩ ዌብሳይት፡ https://yayawallet.com/
    - 1.6 ይህ መግለጫ እስከተዘጋጀበት ድረስ የአክሲዮን ማህበሩ የተፈረመ ካፒታል፡- 75,033,000
    - 1.7 ይህ መግለጫ እስከተዘጋጀበት ድረስ የአክሲዮን ማህበሩ የተከፈለ ካፒታል፡- ብር 50,033,000
2. **<u>የ2ኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች</u>**
    - 2.1 የጉባዔውን አጀንዳዎች ማፅደቅ፣
    - 2.2 የዳይሬክተሮች ቦርድ እ.ኤ.አ 2024/25 የሒሳብ ዓመት ዓመታዊ ሪፖርት ማዳመጥ እና ተወያይቶ ማፅደቅ፣
    - 2.3 የውጭ ኦዲተር እ.ኤ.አ የ2024/25 ሒሳብ ዓመት ዓመታዊ ሪፖርት ማዳመጥ እና ተወያይቶ ማፅደቅ፣
    - 2.4 የጉባዔውን ቃለ ጉባዔ ተወያይቶ ማጽደቅ፣
3. **<u>የ1ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች</u>**
    - 3.1 የጉባዔውን አጀንዳዎች ማፅደቅ፣
    - 3.2 የአክስዮን ማህበሩን ካፒታል ማሳደግ፣
    - 3.3 የአክሲዮን ማህበሩን መመስረቻ ጽሁፍ ማሻሻል፣
    - 3.4 የአገልግሎት ጊዜታቸው ያለቀውን የቦርድ አባላት በሌላ ቦርድ መተካት፣
    - 3.5 የጉባዔውን ቃለ ጉባዔ ተወያይቶ ማጽደቅ፣

<u>ማሳሰቢያ፦</u>

- ❖ የአክስዮን ማህበሩ ሰራተኛ ለባለአክሲዮኖች ተወካይ በመሆን በጉባዔው ላይ መሳተፍ የማይቻል መሆኑን እያሳወቅን፣ለአንድ ባላክሲዮን በማህበሩን ጠቅላላ ጉባዔ በማንኛዉም ችሎታ መወከል የሚችለዉ አንድ ሰዉ ነዉ፡፡
- ❖ በልዩ ሁኔታ በአካል በጉባዔው የምትገኙ ባለአክስዮኖች ማንነታችሁን የሚገልጽ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ እንዲሁም ብሔራዊ መታወቂያ፣ባለአክስዮኖች በመውከል በስብሰባዉ ላይ የምትሳተፉ ተወካዮች የወካያችሁን እና የእናንተን ማንነት የሚገልጽ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት እና የዉክልና ሰነዱን ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ ይዛችሁ እንድትቀርቡ በአክብሮት እናሳስባለን፡፡

**ያያ የክፍያ ስርዓቶች አ.ማ የዳይሬክተሮች ቦርድ**

ያያ የክፍያ ስርዓቶች አማ
YaYa Payment Instrument SC
YAYAWALLET.COM